ግዜ
ግንቦት 7 ዜና
የግንቦት 7 ድምጽ
www.ginbot7.org

ቀን ግንቦት 25 2000 ዓ.ም

ያበደ ውሻ ሁሉን ይለክፋል፣ አሳፋሪው የወያኔ ድርጊት በኮሌጅ ምሩቃን ላይ፣

የግንቦት7 ዜና ክፍል፣ ከመቀሌ ዩኒቨርስቲ የደረሰው ዜና እንደሚያመለክተው፣ የዘንድሮ የዩኒቨርስቲ ተመራቂዎች በሃገራቸው ስራ አግኝተው ለመኖር ከፈለጉ የወያኔ/ኢህአዴግ የአባልነት ቅጽ መሙላት እንዳለባቸው የተነገራቸው መሆኑን ነው። በእዚህ አግባብነት በሌለው አይን አውጣ ጥያቄ የተደናገጡ በርካታ ተማሪዎች ለቤተሰቦቻቸው ስልክ በመደወል የቀረበላቸውን አሳፋሪ ጥያቄ በመግለጽ የቤተሰቦቻቸውን ምክር ጠይቀዋል። ቤተሰቦቻቸውም በህዝብ የተተፋው ወያኔ/ኢህአዴግ ልጆቻቸውን ያለፍላጎታቸው ስራን ማስገደጃ በማድረግ አባላት ሆነው የጥላቻው ሸክም ተካፋዮች ለማድረግ የሚያደርገው ሴራ ቢያናድዳቸውም ለልጆቻቸው ምክር ለመስጠት ያልቻሉበት ሁኔታ እንዳለ የግንቦት7 ዜና ክፍል ለመረዳት ችሏል።

የግንቦት7 ዜና ሪፖርተር እንደሚለው ከሆነ፣ በግንቦት 97 ብሄራዊ ምርጫ ወያኔ/ኢህአዴግ በህዝብ ተተፍቶ ከተሸነፈና በአይነ ደረቅነትና በጉልበት ስልጣን ላይ ለመቆየት ከወሰነ በኋላ፤ ሌላ የስልጣን እድሜውን ለማራዘም እየተከተለ የሚገኘው ስልት ገበሬውን በመሬቱ፣ የመንግስት ሰራተኛውን፣ የኮሌጅ ምሩቁን በስራው፣ ነጋዴውን በብድር አለማግኘትና በታክስ ማብዛት እያስፈራራ፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ግለሰቦችን የድርጅቱ ቅጽ እንዲሞሉ በማድረግ ህብረተሰቡን የወያኔ አባል በሆኑና ባልሆኑ ግለሰቦች በመከፋፈል እርስ በርሱ እንዲናከስ ማድርግ ነው። የዩኒቨርስቲ ምሩቃንንም ካለፈው አመት ጀምሮ ከምረቃ በፊት በስራ በማስፈራራት የአባልነት ፎርም ሲያስሞላ ዘንድሮ የመጀመሪያው እንዳልሆነ ገልጸዋል። ባለፈው አመት በተመሳሳይ መንገድ ምሩቃን ፎርም እንዲሞሉ ተደርገው፣ የተወሰኑት ተመራቂዎች በተለያዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ልክ በደርግ ግዜ ይደረግ እንደነበረው፣ ስራ ኖረም አልኖረም መደልደላቸው ታውቋል።

በሌላ በኩል ግን በየአመቱ ከዩኒቨርስቲዎች የሚመረቀው ተማሪ ቁጥርና ያለው የስራ እድል የማይመጣጠን በመሆኑ የተነሳ፤ ተማሪዎች እሺ ብለው የአባልነት ቅጽ ቢሞሉም፣ በጣት ለሚቆጠሩ የስርአቱ ዋና አቀንቃኞች ካልሆኑ በስተቀር የሃገሪቱ ኢኮኖሚ ድቀትና የመንግስት ባጀት እጥረት፣ የተቀረውን በብዙ ሺህ የሚቆጠር ምሩቅ ስራ ሰጥቶ፣ ደሞዝ መክፈል የማይችል መሆኑን ተማሪዎቹ እራሳቸው የሚያውቁት ጉዳይ እንደሆነ የግንቦት7 ዜና ክፍል ለመረዳት ችሏል።

ወያኔ/ኢህአዴግ 4 ሚሊዮን አባል አለኝ፣ አራት ሚለዮን ተወዳዳሪ አቅርቢያለሁ በማለት የሚመጻደቅበት የተጋነነ የአባላት አሃዝ የተገኘው እንደ ተማሪዎቹ በግድ ቅጽ እያስሞላ የመዘገበውን በሙሉ ቆጥሮ መሆኑን የግንቦት7 ዜና ሪፖርተር ገልጽዋል። በእዚህ መንገድ በኑሮውና በስራው ተገዶ አባል የሆነ ሁሉ ያለፍላጎቱ ያዋረደውን ኢህአዴግ አምሮ የሚጠላ፤ ውርደቱን ለመበቀል ያደባ የተቃዋሚዎች ደጋፊ እንጂ፣ የወያኔ አገልጋይ ከቶውንም እንደማይሆን ታዛቢዎች መግለጻቸውን ሪፖርተራችን በዘገባው አክሎበታል። ይህ አይነት የአባላትን ቁጥር በግድ በማብዛት የህዝብ ተቀባይነት መለኪያ ለማድረግ መሞከር ቀድም ሲል ለደርግ ኢሠፓም እንዳልሰራ ወያኔ ውስጥ ያሉ ኢሠፖዎች የሚያውቁት ጉዳይ ነው ሲሉ አንድ አንድ ታዛቢዎች ይናገራሉ። ህዝቡም በጣም በርካታ ግለሰቦች ተገደውና ማስፈራሪያ ደርሷቸው የአባልነት ቅጽ የሞሉ መሆናቸውን በመረዳት፣ ይህም ህብረተሰቡን እርስ በርሱ ለመከፋፈል ታስቦ የተጠነሰሰ ሴራ መሆኑን በማወቅ፣ በእዚህ መንገድ ተገደው አባል ከሆኑት

ጓደኞቹና ዘመዶቹ ጋር የማይጣላና የማይቃቃር መሆኑን በተግባር እየገለጸ ነው በማለት ሪፖርተራችን ዘግቧል፡፡

በእዚህ መንገድ ተገደው የወያኔ/ኢህአዴግ አባላት ለሆኑት ግለሰቦች ህዝብ የሚያስተላልፈው መልእክት፤ ‹ወያኔን ከውስጡ ሆናችሁ ምስጢሩን አውጡበት፣ ሌብነቱን ክህደቱን የአድሎና የዘረኛነት ስራውን በማስረጃ ደግፋችሁ አጋልጡት፣ ህዘብን ለመሰለል፣ በህዝብ ላይ አደጋ ለመጣል ሲያሴር አስቀድማችሁ ለህዝብና ለህዝብ ወጎኖች መረጃ አስተላልፉ፣ ድሮም ቢሆን ሃገር ሲወረር የውስጥ አርበኛ ከጠላት ካምፕ ገብቶ ይሰራ ነበርና እናንተም ይህን ስራ በመስራት ሃገራዊ ግዴታችሁን ተወጡ፤ ለእዚህ ደርጊታቸሁ የአርበኛነት ሽልማት እንጂ የህዝብ ጥላቻ አታተርፉም፡፡ አትፍሩ አትስጉ እኛ አንጠላችሁም፡፡ ውሎ አድሮ የሚጠላቸሁ ወያኔ እራሱ እንደሚሆን እናውቃለን፡፡ በህዘብ ላይ ከፍተኛ መከራና ስቃይ የሚያዘንቡትን የወያኔ/ኢህአዴግ እውነተኛ ሰላዮችና ገዳዮች ከእናንተ መለየት አያቅተንም፣ የሚል መሆኑን የግንቦት7 ዜና ለመረዳት ችሏል፡፡